የምፅዓቱ የምሥራች

ቅጽ 84 ቁጥር 3(981)

“እምላክ ሆይ ፥ከዘላለም እስከ ዘላለም ተባረክ ታላቅነትና ኃይል ክብርም ለእንተ ነው። 1 ዜና. 29፥11

አምላካችን ታላቅ ነው። (በቻርለስ ስፐርጅን)

“እግዚአብሔር ኃያል ነው ማንንም አይንቅም” (መጽሐፈ ኢዮብ 36፥5)

የእግዚአብሔር ታላቅነት በሰው አእምሮ ሊለካና ሊወሰን የማይችለውን የእግዚአብሔር ቃል የሆነው ቅዱስ መጽሐፍ ያረጋግጣል። (መዝሙረ ዳዊት 62፥11)

ከእግዚአብሔር እጅግ ብዙ ሊቆጠር ከማይቻለው ታላቅነቱ ውስጥ ጥቂቱን ብቻ ከቅዱሳት መጽሐፍት እናገኛለን። (ኢዮብ 26፥ 14)

ለእግዚአብሔር የሚሳነው አንዳች የሌለ ሲሆን ኃይልም ሆነ ሁሉንም ነገር በራሱ በእግዚአብሔር የተፈጠሩ ናቸው። (ዘፍጥረት 1፥1፣ ሉቃስ 1፡37)

በምድራችን በእግዚአብሔር ቤት ሳይቀር ኃያል ታላቅ የተባሉ ሲደክሙ ሲሳሳቱ ያነበብን በሕይወታችንም የተመለከትን ሲሆን እግዚአብሔር ግን በሕያው ቃሉ እንደተረጋገጠው ምን ጊዜም አይደክምም፣ አይሳሳትም ይህ የአምላክነቱ ልዩ ባህርይና መግለጫ ነው።

እግዚአብሔር ሁሉን አዋቂ ሁሉን ቻይ በሁሉም ሰፍራ የሚገኝ ለመሆኑ ቅዱስ ቃሉ ያረጋግጣል። (መዝሙረ ዳዊት 147፥5፣ 96፥10፣ትንቢት ኤርሚያስ 23፥23)

እንዲህ ያለ ታላቅ ኃያል ሁሉን ቻይ አምላክ ለትልቅ አገልግሎቱ የሚጠራቸው የሚሾማቸው ታላቅ ሰለሆኑ ሳይሆን ታናሹቹን ታላቅ በማድረግ ነው።(1 ቆሮንቶስ 1፥26)

በሰዎች ፊት ታላቅ የተባሉትን ሳይሆን ሰዎች የናቋቸውን ጌታ ለከበረ አገልግሎቱ በመለየት ታላቅ እንዳደረጋቸው እንደ ልቤ ብሎ ከበግ እረኝነት ለንጉሰነት ካበቃው ንጉሰ ዳዊት ጀምሮ በምድራቸው እንደምናምንቴ ከተቆጠሩት ከሐዋርያቱና በቤተክርስቲያን ታሪክ በታዩት አማኝ ልጆቹ መጠራትና አገልግሎት የሚታይ ነው። እርሱ ታላቁ ጌታ እግዚአብሔር እኛ ደካሞቹን ሳይንቅ ከውድቀት አንስቶ ክብር እንደሰጠን እኛም ሌሎችን ሳንንቅ የእግዚአብሔር ፈለግ የጌታን ምሳሌነት ተከትለን እንሰማራ (1 ዮሐንስ 2፡6)።

መልዕክት ከአሳታሚው (ሪች ካርማይክል/Rich Carmichael)

“ዕረፉ እኔም አምላክ እንደሆንሁ እወቁ” (መዝሙረ ዳዊት 46፥10)

እጅግ አስፈላጊ ከሆኑት ጉዳዮች ውስጥ አንዱ እግዚአብሔርን በማወቅ አምላክነቱንም በመረዳት በእርሱ ማረፍ ነው። እግዚአብሔር የሁሉ ፈጣሪ ሁሉን ቻይ መሆኑን ባለመረዳት በገዛ ፈቃዳችን በገዛ ችሎታችን የእርሱን ሥራ ለመሥራት መሞከር መጣጣር እጅግ መሳሳት ነው። እግዚአብሔር በጎና መልካምን ነገር በእኛ ማድረግም መፈጸምም መጀመርም እንደሚችል ተረድተን በእርሱ ካረፍን በኋላ እርሱን በጸሎት ጠይቀን ብንሰማራ በአገልግሎታችን ፍሬያማ እንሆናለን።

በእግዚአብሔር ቃል ተመርተን እግዚአብሔር የሚከበርባቸውን ሥራዎች በሚቀጥሉት ሰምንት ነጥቦች እንቅሰቃሴያችንን ለማካሄድ እንጣር።

1. ለእግዚአብሔር ፈቃድ እንገዛ በእግዚአብሔር በመፈጠራችን የፈጠረንን ጌታ ዘላለማዊ እቅድ ከእርሱ ቃል ከቅዱስ መጽሐፍ እንረዳ።(ሮሜ 8፡28) በጌታ የተወደድንና የተጠራን ነን።
2. እግዚአብሔር ፍቅር ሰለሆነ ፈቅሩን እንጠይቀው። የምናገለግለውን ነገር ሁሉ በእግዚአብሔር ፍቅር እንፈጽም (1 ዮሐንስ 4፥8) በፍጹም ነፍስና አእምሯችን ጌታን እንከተለው። (ማርቆስ 12፡30)
3. በጌታ ሁልጊዜ ደስ ይበለን ደስ ሊያሰኙን የሚችሉ ጉዳዮች ሁሉ ጊዜያዊና ጠፊ ሲሆኑ በጌታ የሚገኘውን ልዩ ደስታ እንለማመድ። (መዝሙረ ዳዊት 145፥1፣ ፊልጵ 4፥4
4. የእግዚአብሔርን ቃልና የተሰጠንን ተሰፋ ሙሉ በሙሉ እንቀበል እንታመንበት (ሮሜ 4፥21፣ ማቴዎስ 6፥31፣ 1 ጴጥሮስ 5፥ 7)
5. በታላቅ እምነት እንጸልይ አምላካችንና ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቤቴ የጸሎት ቤት ነው ብሉ ያስተማረውንና እራሱም ሳያቋርጥ ይጸልይ የነበረውን በማገናዘብ በትልቅ እምነት በቃሉ ተሞልተን እንጸልይ (ማቴዎስ 21፥13)
6. በጌታ የሕይወት ልምምድ እንሞላ ጌታ ከእናቱ ማህጸን ጀምሮ በመንፈስ ቅዱስ የተጸነሰ የኖረና እስከፍጻሜው ያለፈ የመንፈስ ቅዱስን ህብረት እንከተል።
7. በተሰፋ እንሞላ በማንኛውም ሁኔታ የከፋ ነገር ቢገጥመንም የጌታ ተሰፋ እናሰብ ተሰፋ እንቁረጥ። (መዝሙር 62፡5)
8. እንቀደስ መቀደስ ለጌታ መለየት ነውና ዓለምን ሳንመሰል ሁሌ ለጌታ የተለየን እንሁን (1 ተሰሎንቄ 5፥23፣ 1 ጴጥሮስ 1፥ 15)

የሰዎች ትልቅነት ከእግዚአብሔር ብቻ ይገኛል

(በኤዲ/አደፍርስ ሀብቴ መካሻ) (ሮሜ 8፥31)

የምጽአቱ የምሥራች በሚል መጠሪያ ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ የእንግሊዝኛውን Herad of His Coming ለህዝባችን እየተረጎምኩ ሳቀርብ የተረዳሁት የምሰብከው ትልቁ ጉዳይ ሰዎች በተለይም የሀገሬ ትውልዶች የዘላለም ሕይወትን ከእግዚአብሔር በልጁ በኢየሱስ ክርስቶ በማመን በመንፈስ ቅዱስ ሥራ እንዲድኑ ነው።

የትርጉሙ ሥራ እንዲጀመር ጥያቄውን በ1980ዎቹ ካንሳስ ኒውተን አሜሪካ የላኩት የቅድስት ማርያም የአዲስ አበባ ሰንበት ትምህርት ተማሪዎች መነሻ ጥያቄ ለዚህ ትልቅ ለሆነው የጌታ ትልቅ አገልግሎት እንደበቃን ምስክር ነኝ። ትርጉሙ የተጀመረበት ወቅት ሰምተው በሀሴት የተቀበሉት በዚያው ቅድስት ማርያም አካባቢ የሚገኘው የአዲስ አበባ መካነ ኢየሱስ ወጣቶች ትብብርም ትልቅ ሥራ ነበር።

የትርጉም ሥራውን በሕብረት ለመሥራት የተባበሩት የአዲስ አበባ ንግድ ሥራ ኮሌጅ ምሩቃን የሰነጽሑፍ አገልጋዮች ቀጣይ ትብብርም ትልቅ ነው።

በሀገራችን የክርስቶስ ተከታይ መሆናቸውን ከሚመሰክሩት ውስጥ ልዩነቶች ቢኖርም ሌሎችን አቅፎ በመቀበል ትልቅ ምሳሌ የሆኑኝ ሳገኛቸው የባረኩኝ የትግራይ ሊቀጳጳስ አቡነ መረሀ ክርስቶስም የታላቅነት ድርሻ ይወሰዳሉ።

እንግዲህ ምን እላለሁ የኃይሉ ባለጠግነት በእኔ በደካማው እንዲገለጥ ከትቢያ አንሰቶኝ ከትውልድ ሀገሬ ተሰድጄ ባለሁበት አሜሪካ ሌሎች ዜጎች ኔፓሎች አፍጋኒስታኖች አፍሪካውያን ላይቤሪያኖችና ሴራሊዮኖች የኤርትራና ሱዳን ዜጎች ጭምር በወንጌል እንድንደርስ ቅዱስ ጥምቀቱን እንዲቀበሉና እንዲድኑ ይህን ታላቅ የወንጌል አገልግሎት ያስጀመረኝ ያስቀጠለኝ ጌታ ክርስቶስ ይክበር። ደጋፊ ባለቤቴን ፋንታዬ ግርማና ልጆቼን ከእድሜና ጤንነት ጋር ለሰጠኝ ጌታዬ ታላቅነት በቃላት የማይገለጸው ምስጋናና ክብሩን

አውጀለሁ። በተቀደሰችው የብሰራት ወንጌል ራዲዮ በልጅነት ወንጌሉን ያስሙኝ አገልጋዮችን ትውልድ ጌታ እንዲባረክ ጸሎታችሁን እየጠየቅሁ ይህን የወንጌል መነቃቃት አገልግሎት በጸሎት በሚቻላችሁ ትደግፉ ዘንድ በጌታ ፍቅር እጠይቃለሁ። ቄስ ቻፕሊያን ኤዲ/አደፍርስ ሀብቴ መካሻ “እንግዲህ ስለዚህ ነገር ምን እንላለን እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ …” ሮሜ 8፥31

የፍቅር አምላክ እግዚአብሔር (በኦክታቢስ ዊንስሎ)

“እግዚአብሔር ፍቅር ነው” (ዮሐንስ 4፥16) እንዱ የእግዚአብሔር እንጸባራቂ ገጽታ ማዳኑ ሲሆን ሌላው ደግሞ እቻ የሌለው ፍቅሩ ነው።

የእግዚአብሔር ልዩ ባህርይ የማታየው በገለጠልን ልዩ ፍቅሩ ነው። እንዲህ ያለ በቃላት ሊገለጽ የማይችል ፍቅር እግዚአብሔር የገለጸ ቢሆንም ይህንን ፍቅሩን የሚቀበሉት አነስተኛ ቁጥር ያላቸው መሆኑ በዘመናት ሁሉ ይታያል። ይህን ልዩ የእግዚአብሔር ፍቅር ችላ ማለትና በእምቢታ ጸንቶ ለዘላለም ቁጣ ለሰይጣንና ለተከታዮቹ ለተዘጋጀው መዳረግ ምን አይነት አሳዛኝ ፍጻሜ ነው። (ማቴዎስ 25፥4)

ፍቅር የእግዚአብሔር መግለጫ ብቻ ሳይሆን ራሱ እግዚአብሔር ፍቅር ነው:: (ዮሐንስ 4፥16)

የእግዚአብሔር ፍቅር በልዩ ሁኔታ የተገለጠው በአንድያ ልጁ በጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ህይወት አገልግሎትና በመስቀል ሞቱና በትንሳኤው ሕያው መልዕክት ነው። (ሉቃስ 24፥26)

እግዚአብሔር ፍቅር የሚታይበት አምላክ ብቻ ሳይሆን የፍቅር ምንጭ ፈጣሪና ሰሪ ነው። ብዙ ኃይማኖቶች አምላኮቻቸው እንደፈራጅ እንደቀጭ በማድረግ በጭንቀት ሲከተሉት የክርስትናው አምላክ ግን ጌታና አምላክ ሰውም በሆነው በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ከቅድስት ድንግል ማርያም በተወለደው አማካኝነት አፍቃሬ አባት ሆኖልናል። ማንም ኃይማኖት መሪ ተከታዮቹን ልጅ ብሎ የማይቀበል ሲሆን የእኛ የክርስቲያኖች አምላክ ግን በደላችንና ኃጢያታችን ሳይገድበው ልጆች ብሎ ሲጠራን ሲቀበለን ሲያድነንና ከጥፋት ሊመልሰን እንመለከታለን። (ሮሜ 8፥16)

በሰው ልጆች ታሪክ ከፍተኛው ፍቅር የታየበት የአምላክ የፈጣሪ ፍቅር በአንድ ልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ የተገለጠውን ይህን ፍቅርና አባትነት ላላገኙ ላላመኑ ሁሉ እንመሰክር፣ እኛም እንደ ፍቅር ልጆች እንመላለስ።

እግዚአብሔር ያፈቅረናል (Wesley Duewel/በዌስሌ ዱዌል)

እግዚአብሔር ለእያንዳንዳችን የገባልንና ያሰበልን ልዩ ሰጦታው ፍቅሩ ነው። የሰዎች ብዛት ሳይሆን የእግዚአብሔር የማይሻር ቃል እንደሚለው እግዚአብሔር እኛን አማኝ ልጆቹን በማይለወጥ የዘላለም ፍቅር እንደወደደን ቅዱስ ቃሉ ያረጋግጣል።

እግዚአብሔር ሰዎችን እንደሚያፈቅር የገለጸበት መንገድ አንድልጁን በወደደበት መልኩ መሆኑን ያረጋግጥልናል። (ዮሐንስ 15፥9)

ይህ ምን ዓይነት ተዓምር ነው? የእግዚአብሔር ተፈጥሮና ማንነት ፍቅር መሆኑን ራሱ ይነግረናል ቅዱስ ቃሉም ይህን ያረጋግጣል። (ዮሐንስ 17፥ 24)

እግዚአብሔር ፍቅሩን ለሰው ዘር በፍጥረት ጀምሮ እየገለፀና እያሳየ ለዛሬው ዘመን ደርሰናል። ይህ ፍቅሩም አምላክም ሰውም ሆኖ በተገለጠው ዘላለለም ያው በሆነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተረጋግጧል። (እብራውያን 13፡8)

የእግዚአብሔር ፍቅር ከእግዚአብሔር ወደ ሰዎች ከሰዎችም ወደሰዎች የሚተላለፍ የሚቀጥል ነው። መጀመሪያ እግዚአብሔር

ሰውን ሰለሚያፈቅር በእራሱ አምሳያ ፈጥሮታል። ሆኖም ግን የሰው ዘር በሰይጣን አሳሳችነት ከፈጣሪው ሲለይ እግዚአብሔር ወዴት ነህ ብሎ ፈልጎታል። (ዘፍጥረት 3፥9)

በዘመን ፍጻሜም የሰው ዘር በሰይጣን አለምና በሰጋ አሳችነት በደሉ በዝቶ ከእግዚአብሔር ቢለይም ፍቅር የሆነው እግዚአብሔር አንድ ልጁ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን በነበረው የብሉይ ሕግና ሥርዓት መሠረት የበጎችና የፍየሎች ደምና መሰዋዕትነት ሊፈጽመው ያልቻለው በኢየሱስ ክርስቶስ በአዲስ ኪዳን በግ በሆነው በኩል ለሰው ዘር ሁሉ ብቸኛ ቤዛ ሆኖ ተገልጧል። (ማርቆስ 10፥45፣ ሉቃስ 2፥28)

እግዚአብሔር የሰው ልጆችን አስቀድሞ እንደሚያፈቅርና እንደሚያድን ቀድሞ የተገለጸ ሲሆን ይህም የተሰፋ ቃል በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ተከታዮች በቅዱስ ቃሉ ምስክርነት የጸና በቤተክርስቲያን ታሪክም የቀጠለ የክርስትና መሠረታዊ ጉዳይ ነው። (ወደ ኤፌሶን ሰዎች 1፥4)

እግዚአብሔር እንደሚያፈቅረን ትልቁ ዋቢ ማሰረጃ ህያው ቅዱስ ቃሉ ነውና በቅዱስ ቃሉ የእግዚአብሔርን ፍቅር ለራሳችን በማሳወቅ ለሰዎች ሁሉ ይህ ልዩ ዘላለማዊ ፍቅር በዚህ ፍቅር በጠፋበት ዘመናችን እንመስክር፣ እናስተምር፣ እንኑርበት።

የእግዚአብሔር ተሰፋዎች ጥቅም (በኤ ቶዘር/A Tozer)

የዘላለም አምላክ እውነተኛ ፈራጅና ገዥ አምላክ ተሰፋዎችህን በዚህ ወቅት ይህንን ተሰፋህን ግለጥልን አሜን!

የእግዚአብሔርን ተሰፋዎች በቃሉ የሰጠንን አበክረን ልንጠይቅ ልናስላስል፣ ልንጠቀምና ልንኖርበት ያስፈልገናል። የእግዚአብሔር ተሰፋ በተጨባጭ የምናውቀውና የምንኖርበት እኛ ከእግዚአብሔር ጋር በቅዱስ ቃሉና በጸሎት ስናቀራርብ ነው። (ዘፍጥረት 28÷16) ያእቆብ በዚህ ሥፍራ በእርግጥ እግዚአብሔር አለ ብሎ እንደመሰከረ እኛም ከእግዚአብሔር ጋር በጽኑ ከተሟገትን ከማለድን የእግዚአብሔርን መገኘት እናረጋግጣለን።

በኃይማኖት ሥርዓት ብዙ የእግዚአብሔር ተሰፋዎች ቢሰጡም በትክክል የእግዚአብሔርን ተሰፋ ለግል ሕይወታችን የምንቀበለው በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በእምነት በእግዚአብሔር ጸጋ ስንኖር ነው። (ዮሐንስ 1፥ 12)

በዘመናችንም ሆነ በቀድሞው ዘመን የነበሩ የእግዚአብሔር ሰዎች የእግዚአብሔርን ተሰፋዎች እንዳያገኙ ትልቁ እንቅፋት ኃጢያትና ጭንቀት ናቸው። ለኃጢያት መንፈስ ቅዱስ በገለጠልን ልክ በንሰኃ ለጌታ ማሰታወቅ ሲሆን ለጭንቀትም ማሰወገጃው የሚያሰጨንቁንን ነገር ሁሉ ለጭንቅ አሰወጋጁ ጌታ ማሰረከብ ነው። (1 ጴጥሮስ 5፥7) ጌታ ሆይ ጭንቀታችንን እንሳልን አሜን!

ሰዎችን ከእግዚአብሔር የሚለየውን ኃጢያት ለማሰወገድ ብቻ መንገድ ኃጢያታችንን እንደልማድ በመቁጠር ወይም ሁሉም ያደርገዋል ብለን በሌሎች በማላከክ ሳይሆን ምንም ሳንዋሸ ለጌታም ለራሳችንም እውነተኛ በመሆን በንሰኃ መመላለስ መስተካከል ነው። (1 ዮሐንስ 9፥

እግዚአብሔር በዘመናት ሁሉ የማይለዋወጥ ትናንት የእግዚአብሔር ምሳሌ የነበረ የአይሁድ የእሰራኤል ሕዝብ ከክፉ ኃጢያት በነቢያቱ በኩል በምህረት እንደጎበኛቸው በአዲስ ኪዳን በሐዋርያቱ በኩል በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሰም ሰርየትን እንደሰጣቸው ዛሬም የያዘንን የከበበንን ማንኛውንም ኃጢያት በኢየሱስ ክርስቶስ ሰም በሚደረግ ጸሎት እግዚአብሔር ሊያሰተሰርይልን ሊያነጻን ሊምረን የሚችል ሁሌም ለዘላለም የማይለወጥ አምላክ ነው “እኔ እግዚአብሔር አልለወጥም”(ትንቢተ ሚልክያስ 3፥6) የተሰፋ ቃሉ በእግዚአብሔር ዘንድ ዛሬም አለ።

የእግዚአብሔር የሆነ ሕዝብ ብቻ ታላቅ ነው

ብዙ ሀገሮች በዜጎቻቸውና በታዋቂ ደራሲያን ታላቅ ሀገር ሲባሉ በታላቅነት ትርክት ትእቢት በመሞላት ሌሎችን ሲወርሩ ሲጨቁኑ ሲያፈርሱ በታሪክ ታይተዋል። እውነተኛው ታላቅ ሕዝብና ሀገር ግን የእግዚአብሔርን ታላቅነት በእንደበት በእዋጅና በተግባር የሚፈጽም ሀገርና ሕዝብ ነው። (ኢሳይያስ 41፥10)

በክርስትና ሕይወት እንዱና ትልቁ ነገር የእግዚአብሔር ሕዝብ በመሆን ታላቅነቱን እንደትልቅ ሕዝብ መመሰከርና ለመኖር መቻል መጣጣር ነው። “ታልቅ ሕዝብ ነን ሃሌሉያ በከበረው ደሙ የተዋጀን” ብለን የዘመርነው በእርሱ በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደም የተቤዠን ታላቅነት ያገኘን ሕዝቦቹ ስለሆን ነው። : ትልቅነታቸውን እያወጁ ከፈጣሪ በላይ እራሳቸውን ከፍ ለማድረግ የጣሩ መሪዎች ሁሉ ተራ በተራ በውርደት ሲወድቁ ሲፈርሱ በታሪክና በቅዱሳት መጽሃፍት እይተናል።

የእግዚአብሔር ታላቅ ሕዝብና ሀገር ለመሆን እንደ ቅዱስ ቃሉ መኖር መመላለስና ማድረግ የሚከተሉትን ያካትታል ያጎናጽፋል።

1. ለእግዚአብሔር ፈቃድ መገዛት በእግዚአብሔር የተፈጠርን በመሆናችን ለእግዚአብሔር ዘላለማዊ እቅድ መገዛት መታዘዝ ይኖርብናል።(ሮሜ 8፥28)
2. እግዚአብሔርን መውደድና መታዘዝ እግዚአብሔር ፍቅር ነው እግዚአብሔር እርሱ አስቀድሞ ስላፈቀርን እኛም ከእግዚአብሔር የተነሳ በክርስቶስ ልጅነት ስላገኘን የፍቅር ልጆች ነን። (1 ዮሐንስ 4፥ 8፣ ማርቆስ 12፥30)
3. በእግዚአብሔር ደስ ይበለን እውነተኛ ደስታ የምናገኘው ከእግዚአብሔር ብቻ ነው። ትውልድ ሁሉ በእግዚአብሔር ሲገኝ ደስታ አለው። መዝሙረ ዳዊት 145)
4. እግዚአብሔርን እንደቃሉ እንመነው እግዚአብሔር የሚታመን አምላክ ነው። እግዚአብሔርን ያመኑ ዘላለም ይኖራሉ። (ሮሜ 4፥20፣ ማቴዎስ 6፥31)
5. ጸሎታችን በእምነት ይሁን እግዚአብሔር ጸሎትን የሚሰማው በእምነት ስለሆነ በቃሉ መሠረት በእምነት እንጸልይ። (ኤፌሶን 3፥ 20)
6. በእግዚአብሔር ተስፋ እንሞላ ተስፋ ትልቅ የእግዚብሔር ሰጦታ ስለሆነ በእግዚአብሔር ተስፋ ይኑረን። (መዝሙር 42
7. ቅዱሳን ሁኑ - (1 ጴጥሮስ 1፥15)
   ተቀደሱ (1 ተሰሎንቄ 5፥23)

ሸክምን ወደ ዝማሬ ስለመቀየር (በዋልተር ቢውተር)

በትንቢተ እምባቆም መልክት ለዛሬው ዘመን ክርስቲያን እጅግ የሚጠቅም የትንቢት ቃል ነው። የነብዩ እምባቆም ሸክም በዘመናት ሁሉ በእግዚአብሔር ቤት ሥራ መልካም የአዝመራ ፍሬ ውጤት እንዲገኝ ለሚተጉ ለሚጸልዩ ለሚደክሙ ተስፋ እንዳይቆርጡ ጌታን እስከመጨረሻ እንዲጠብቁ የሚያሰተምር የሚያጽናና ቃል ነው። “እምባቆም ያየው ሸክም ይህ ነው” (ትንቢተ እምባቆም 1፥1)

በእምባቆም ዘመን በጌታ ቤት እደባባይ ሊገኙ የሚገባቸው መልካም ሥራዎች ፍሬዎች ባለመገኘታቸው ነብዩ እጅግ አዝኖ እንደነበር ዛሬም የእግዚአብሔር ቤት ተብለው በሚታወቁት ዘንድ የእግዚአብሔር መለያ የሆኑ መልካም ሥራዎችና ውጤቶች እያጠፉ ብዙዎችን እያሳዘኑ ይገኛል። በዚህ ውድቀትና መክሸፍ እኛ የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃል የምናምን ተስፋ ቆርጠን ልንተው ወደኋላ ልንመለስ ሳይሆን ነብዩ እንዳሳሰበን ፍሬዎቹ በጎቹ ላሞቹ ባይገኙም በጌታ ከማመን ከመታመን በፍጹም ወደ ኋላ አንልም። (እምባቆም 3፥18)

በጌታ ቤት በቃል በዝማሬ በሰደቱ ዘመን መከራ ቀድሞ የተጉ ዛሬ ፍሬ አልባ ቢሆኑ በዘመን አመጣሽ ዓለማዊ ፍልሰፍና በክፉ የባለጠግነት ምኞት በምትሃታዊ መሳይ መገለጦች ቢወሰዱም እኛ የመሰቀሉ ቃል የገባንና የምናምን በምንም በማንም ተሰፋ ሳናደርግ እምነታችንና ተሰፋችን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ በማድረግ ሸክማችንን ለጌታ እናሰረክባለን ሸክማችን ወደ ድንቅ ዝማሬ ይለወጣል።

በባሪያ ፍንገላው ዘመን በባርነት ሸክም የነበራት ሴት የባሪያ ፋንጋዩ ግፍ ከሀገር ከምድሩ መሰደድ ተሰምቷት በአፍሪካ ቋንቋ የዘመረችው Amazing grace አሰደናቂ ጸጋ ባርያ ፈንጋዩ ጆን ኒውተን ልብ ነክቶ የባርነት ሥራውን እርግፍ አድርጎ በመተው የወንጌል ሰባኪ ሲሆን ያ ዝማሬ ዛሬም ድረስ ከ400 ዓመታት በኋላ ኃያል ድንቅ ዝማሬ በሀገራችን በሰደቱ ዘመን የተዘመሩ ድንቅ ዝማሬዎችም የሸክም በዝማሬ መቀየር ምሳሌ ናቸው።

ዓለም አቀፍ ምስክርነቶችና የጸሎት ርዕሶች

ዓለም አቀፍ ምስክርነቶች

<u>ከዩጋንዳ (አፍሪካ)</u>

የምጽዓቱ የምሰራች አገልግሎት ለዘመናት በመንፈሳዊ ሕይወቴ ደጋፊ ሆኖኛል እግዚአብሔር ይባርካችሁ።

<u>ከቬትናም (እሰያ)</u>

በየምጽዓቱ የምሥራች የተነሳ የጌታን መንገድ አግኝቻለሁ ተባረኩ!

<u>ከእንግሊዝ</u>

በታማኝነት ለብዙ ዓመታት ጋዜጣውን ሰለምትልኩልኝ ከልቤ አመሰግናለሁ። እግዚአብሔር አብዝቶ ይባርካችሁ።

<u>ከመካከለኛው ምሰራቅ</u>

የምጽዓቱ የምሥራች በዚህ በአሰጊ አካባቢ ትልቅ መጽናኛዬ ነው። ሳታቋርጡ ላኩልኝ። የአቅሜን ሰጦታ በሚቀጥለው ወር እልካለሁ።

<u>ከካናዳ</u>

በየምጽአቱ የምሥራች ሰለሚቀርብልን የተቀቡ መልእክቶች ጌታን አመሰግናለሁ ሁሌ የማነበው ጋዜጣ ነው። በጣም እወደዋለሁ።

ዓለም አቀፍ የጸሎት ርዕሶች

<u>የአሜሪካ የኮሌጅ ሕብረቶች እድገት</u>

በአሜሪካ በሚገኙ ኮሌጆችና ዩንቨርሲቲዎች የወንጌል ማዳረሰ በመገሰገሰ ላይ ነው። ከ2015 ጀምሮ ከ100 ሺ በላይ የኮሌጅ ተማሪዎች በወንጌል ተደርሰዋል። ጌታን ሰለዚህ ድንቅ ሥራ እናመሰግን በዚህ አሰቸጋሪ ዘመን በኮሌጅ የሚያገለግሉ እንጸልይላቸው በሚቻለንም በገንዘብ እንርዳቸው።

<u>የሶርያና የሊብያ ሰደተኞች</u>

ድሮ ከሀገራቸው የማይወጡ የሶርያ ሰደተኞች በሀገራችን ኢትዮጵያ ጎዳናዎች ሳይቀር ሲለምኑ እንመለከታለን። ለእነዚህ ወገኖች የወንጌል ቃል የሚመሰክሩ አገልጋዮች እየተነሱ ነው፤ እንጸልይላቸው፣ እኛም እንመሰክርላቸው።

<u>ለእሰራኤልና ለፍልሰጤም ጸሎት</u>

የእግዚአብሔር ሕዝብ የብሉይ ኪዳን ምሳሌ እሰራኤል ጌታ እንዲያሰባት እንጸልይ። በእሸባሪ ቡድኖች ሰበብ በእሰራኤል ጦር ለሚያልቁ ፍልሰጤሞች ጸሎትና እርዳታችን ይድረሳቸው። እሰራኤል የአዲሰ ኪዳኗ የክርሰቶስ ቤተሰቦች ከሁሉም ዘርና ነገድ የሚገኙ መሆናቸውን እናሰተምር። (ሮሜ 9፥1-5)

<u>መልዕክት ከአሰተባባሪው</u>

ሰለምትሰጡን መልካም አሰተያየት ከልብ እናመሰግናለን። ለእያንዳንዳችሁ መልሰ መሰጠት ሰለማንችል በዚሁ ምሰጋናና ሰላምታችንን እናቀርባለን። ለአግልግሎቱ ብቸኛው ገቢ የአንባቢያን መዋጮ በመሆኑ በፖሰታ አድራሻችን ላኩልን የምጽዓቱ የምሥራች የፖ.ሣ.ቁ 8986፣ አዲሰ አበባ፣ ኢትዮጵያ።

የየእለቱ ከጌታ ጋር የጥሞና ጊዜያችን (በእንድሪው ሙሪ)

“ኅብረታችንም ከአባት ጋር ከልጁም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ነው” (1 ዮሐንስ 1፥3)

በክርስትና የሚኖረን ማንኛውም ህብረት ከጌታና ከአባቱ እግዚአብሔር አንድ አምላክ ጋር ያለ ልዩ ግንኙነት ተምሳሌት ነው።

ህብረታችንን በሀገር በቋንቋ በባህል በእምነት ተመሳሳይነት ማድረግ መልካም ቢሆንም ትክክለኛውን ህብረት ለማግኘት ግን የእግዚአብሔር አብ አባትና የልጁ የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሕብረትና አንድነት ያገኘ ዘንድ መጣር መጸለይ መቃተትና መለማመድ ይገባናል። አብና ልጁ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ያላቸውን ሕብረት ለማግኘት ዋናው ኃይላችን ጌታ አምላክ መንፈስ ቅዱስ ሲሆን ያንንም በብርቱ ጸሎትና በቃሉ እናገኛለን። ያንን ትክክለኛ ህብረት አማኞች እርስ በርሳችን ሰንቀዳጅ የናቁን ያሳደዱን ሊገድሉን የሚፈልጉ ሁሉ ከእኛ ሕብረት ጌታ በሚያፈልቀው የመንፈስ ቅዱስ እሳት ተነክተው ምን እናድርግ ብለው እኛኑ እስከመጠየቅ ይደርሳሉ። “ምን እናድርግ አሏቸው” (ሐዋርያት ሥራ 2፥37)

ጌታ እግዚአብሔር ይህንን ቅዱስ ህብረት ሰጥቶን ሌሎቹን ከጨለማ ወደ ብርሃን የምናመጣበትን ኃይልና ጸጋ ይስጠን።

<u>በሀገራችን ያሉ ኅብረቶች</u>

ይህንን የመንፈሳዊ መነቃቃት የእንግሊዝኛ እትም በማንበብ ትርጉሙ ለሕዝባችን እንዲደርስ ተርጓሚው እንዲጠየቅ ሀሳቡ ያቀረቡ የአዲስ አበባ ቅድስት ማርያም ተዋህዶ ኦርቶዶክስ የሠንበት ትምህርት ቤት ተማሪዎች ህብርት መጥቀስ ይገባል።

ትርጉሙ እንዲቀጥል መነቃቂያና ድጋፍ የለገሱ በዚያው ቅድስት ማርያም አካባቢ የነበሩ የአዲስ አበባ መካነ ኢየሱስ ወጣቶች ህብረት የሚጠቀሱ ሲሆን ትርጉሙ በታይፕ እንዲቀጥል ተርጓሚና አስተባባሪውን የደገፉ የንግድ ሥራ ኮሌጅ ምሩቃን ህብረትም ይመሰገናሉ።

በዚህ ወቅት ትክክለኛ የእግዚአብሔርን ቃል የተከተለ ሕብረት እንዲኖረን ሀገራችን ካለችበት ውጥንቅት እንድትወጣ የሰማይም የምድርም በረከት እንዲበዛልን ትክክለኛ ሕብረት እንዲኖረን ብርቱ ጸሎትና ምልጃ እናቅርብለት።

የእግዚአብሔር ፍርሃት የበረከት ሁሉ ምንጭ ነው

(በጆን(ዮሐንስ) ጊል)

“የነገሩን ሁሉ ፍጻሜ እንሰማ ይህ የሰው ሁሉንተናው ነውና፤ እግዚአብሔርን ፍራ” (መክብብ 12፥13)

የሰው ሁለንተና ተብሎ በጌታ ቃል የተጻፈልን የእግዚአብሔር ፍርሃት እንዲኖረን ነው። እኛ ክርስቲያኖች የእግዚአብሔር ፍርሃት የሚጠበቅብን በጭንቀት በፍርድ ይቀጣናል ብለን በማሰብ ሳይሆን እንደ አባትነት እንደፈጣሪነት እንደተንከባካቢነትና አዳኝነት ፍቅሩን አንድ ልጁን በመሰቀል ሞት ቅጣት አሳልፎ እስከመሰጠት ድረስ ያደረሰው ልዩ ፍቅሩን በማሰብ ነው።

የእግዚአብሔር ፍርሃት ሲበዛልን ኃጢያትን ከእግዚአብሔር የሚለየንን ክፉ እርም እንድንጸየፍና እንድንርቅ ያደርጋናል። (ምሳሌ 8፥13፣ ሮሜ 12፥9) እግዚአብሔርን በምንፈራበት ወቅት ትእዛዛቱን በሚገባ ለማክበር እንበቃለን እንደ እኛው የፈጠራቸው ያዳናቸው የሚባርካቸው ሰዎችን ሁሉ የምናከብር የምናፈቅር እንሆናለን። የእግዚአብሔር ፍርሃት እግዚአብሔርና ሰዎችን የሚያሳዝን ሳይሆን ልዩ ፍቅርና አክብሮትን የሚጨምር ነው። (ዘሌዋውያን 19፥14) የእግዚአብሔር ፍርሃት ሰዎች ሌሎች የሚያደርጉትን ነገር ሁሉ በፉክክር በእልህ እንዳንፈጽም ይጠብቀናል። (ነህምያ 5፥15) የእግዚአብሔር ፍርሃት ሰዎች

ሁለነገራቸውን ለጌታ እንዲገልጡ ያደርጋቸዋል፡ ፡ (ዘፍጥረት 22፥12) የእግዚአብሔር ፍርሃት አማኞችን አዳማዊና ሰጋዊ ሥራዎችን እንዳይፈጽሙ ያበቃቸዋል። (ሮሜ 3፥18) የእግዚአብሔር ፍርሃት ከእርሱ ከእግዚአብሔር ባለብዙ ግርማና ሥልጣን ካለው የሚመነጭ ያመኑ የጠራቸው ቅዱሳን ሰዎች ሁሉ ተጠብቀው እንዲሰማሩ የሚያበቃ ልዩ መለኮታዊ ሥጦታ ነው። (ኢሳይያስ 6፥3-7፣ ሮሜ 3፥7) በዓለማችን ታሪክ ከቅዱሳት መጽሐፍት ጀምሮ ለሰው ዘር ምድራዊና ሰማያዊ መፍትሄ መሣሪያ የሆኑ ሰዎች ሁሉ የእግዚአብሔር ፍርሃት የሰፈነባቸው ጨዋ የትህተትና ሰዎች ናቸው(ሙሴ፣ ኤርሚያስ፣ ኢያሱ ሓዋርያቱና የተሃድሶ መምህራንን ያካትታል)

ማስታወቂያና ማሳሰቢያ

<u>ለየምጽዓቱ የምሥራች ተርጓሚዎች</u>

የአማርኛውን ጭምር በዓለማችን ላይ በ17 ቋንቋዎች ይህን የመንፈሳዊ ጋዜጣ ለሚተረጉሙና ለሚያሰራጩ ብርቱ ጸሎት እናድርግ። በልዩ ልዩ መንገድ ሥርጭቱን የሚገዳደር የክፉ መናፍስት አሰራርን በብርቱ ጸሎት እንፋለም።

<u>በሥራና በትምህርት ተታለው ለሚሰቃዩ እንድረስ</u>

በሀገራችን ኢትዮጵያና በሌሎች ታዳጊ ሀገሮች በአታላይ ደላሎች በሀሰት የትምህርትና የሥራ እድል ማታለያ ለከፍተኛ ሰቃይ ለሚዳርጉት ባህር ለሚጣሉት ራሳቸውን ከሰቃይ የተነሳ ለሚያጠፉት ጌታ እንዲጠብቃቸው እንዲመልሳቸው እንጸልይ። ሀሰተኛ ደላሎችም ለጸጥታና ፖሊስ አካላት በማሳወቅ ወገኖቻችንን እናድን።

<u>ለምህረት አምባ አገልግሎት ድጋፍና ጸሎት</u>

በሀገራችንም የምህረት አምባ በሚል የምጽዓቱ የምሰራች ተርጓሚና አስተባባሪ ከባለቤቱ ፋንታዬ ግርማ ጋር ያቋቋሙትን አገልግሎት በሚቻለን እንደግፍ።

<u>የመዳን መንገዶች</u>

1. ኃጢያተኛ ለመሆናችን የጌታን ቃል በማንበብ ንሰኃ እንግባና እንመነው። (ሮሜ 3፥23፣ 6፥23) 2
2. የእግዚአብሔርን ይቅርታ በንሰኃ ተቀብለን ከክፉ ምገዳችን እንመለስ። (ኢሳይያስ 55፥ 7)
3. በኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝነት ካመነ በኋላ በቅርባችን ወዳለ ቤተክርስቲያን በመሄድ እንሳተፍ።

<u>ለአማርኛው አንባቢዎች</u>

የምጽአቱ የምሥራችን ለአንባቢዎች በነጻ በብዛት ማሰራጨት እንድንችል መዋጮ በፖስታ ቤት አድራሽ በመላክ ተባበሩን ጌታ ሀገራችን ኢትዮጵያን በበረከቱ እንዲጎበኛት ጸሎታችሁ አይቋረጥ ለእኛም ለአዘጋጆቹ ጸሎታችሁ አይቋረጥብን።

ተርጓሚና አስተባባሪ

ቄስ ቻፕሊያን ኤዲ/አደፍርስ ሀብቴ መካሻ
Herald of His Coming/የምጽአቱ የምሥራች የወንጌል መነቃቃት አገልግሎት ዋና አሳታሚ /publisher/ Rich Carmichael

የአማርኛው ተርጓሚና አስተባባሪ - አደፍርስ/ኤዲ ሀብቴ መካሻ

Amharic coordinator Translator - Eddie/Adefrs Habte Mekasha

አርትኦት - መለሰ ሙላቱ

ሰርጭት ብርሃኑ ጥርሰማ
Distributieon Berhanu Tirsema

የአማርኛ አሳታሚ - የምህረት አምባ አገልግሎት ዲዛይንና የጽሕፈት ሥራ - እቤኔዘር የጽሕፈት ሥራ፣ መካኒሳ

ፖ.ሣ.ቁ. P.O.Box - 8986
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
Addis Ababa, Ethiopia
በአንጾኪያ ትርጉምና ጽሕፈት ሥራ ታተመ

በነጻ የሚሰራጭ